# የዓባይ ግድብ የአመለካከት አድማስ ቢሰፋ

ከሞገስ ወርቁ

ዓባይ (Blue Nile) የኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን የታችኛው ተፋሰስ አገሮች ለዘመናት ቁልፍ ጉዳያቸው ሆኖ ቢታይ ሁሉም በቂ ምክንያት አላቸው:: ዓባይ ለአገራችን ከውኃ ያለፈ ትርጉምና ለአገራችን ሕልውናና ውበት ትልቅ ድርሻ ያለው ነው:: በዓባይ ተፋሰስ ውስጥ የሚኖረው የሕዝብ ብዛት በበርካታ ዘገባዎች እንደተመለከተው 25 በመቶ ሲሆን፣ ተፋሰሱ የሚሸፍነው ከአህጉሪቱ የቆዳ ስፋት 20 በመቶ ያህሉን በመሆኑ፣ ተፋሰሱ ያለው ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑን ያመለክታል:: ዓባይ እስከዛሬ ድረስ ከሰጠው ጠቀሜታ አንፃር በየትኛውም መስፈርት ሲታይ ከፍተኛ ተጠቃሚዎቹ የታችኛው የተፋሰስ አገሮች ናቸው:: በተለይም ግብፅ "የዓባይ ልጅ ውኃ ጠማው" እንደሚባለው 59 ከመቶ (ባሮና ተከዜ ሲታከሉበት ወደ ናይል የሚፈሰው የውኃ መጠን ከ80 በመቶ መሆኑን ልብ ይሏል) ያህሉን የናይልን ውኃ የሚያበረክተው የጥቁር ዓባይ ምንጭ አገር ኢትዮጵያ ተጠቃሚነቷ እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም:: ቁርጠኛ አመራር ማጣት፣ የውስጥ አለመረጋጋትና ድህነት የአገሩ ዜጋ ዓባይን በቁጭት ዜማው ሲያማርረው እንዲኖር ተገዶ ነበር::

ዓባይ በአገሩ ሲኮነንባቸው ከነበሩት መለያዎቹ ውስጥ በቢሊዮን ቶን የሚቆጠር ለም አፈር ጠርጎ መውሰዱና ለታችኛው ተፋሰስ አገሮች የማዳበሪያ ወጪ ሳያወጡ በዋናው የወንዙ ተፋሰስ ከፍተኛ ምርት ማምረታቸው፣ የውኃን ተጠቃሚነት ኢ-ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እንዲቀጥል ጥረት ማድረጋቸውና ሁኔታዎች በነበሩበት እንዲቀጥሉ የታችኛው ተፋሰስ አገሮች በተለያየ መንገድ የአገሪቱን ሰላምና ልማት ለመፈታተን የሚቻላቸውን ሁሉ ሲያደርጉ መቆየታቸው ይገኙበታል::

አሁን ባለንበት ዘመን መንግሥታችን ጠንካራ አቋም በመያዝ የቆየውን ኢ-ፍትሐዊ የውኃ አጠቃቀም ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ለመቀየር ያደረገውና እያደረገ ያለው ዘርፈ ብዙ ጥረት ከዓባይ ጋር ለመታረቅና ዓባይን ከጠላትነት ወደ ወዳጅነት፣ ለአገር ክብርና ኩራት እንዲሆን ያለውን መልካም ሐሳብ ያመለክታል:: ለዚህ ደግሞ ትልቁ አመላካች በዓባይ ጉዳይ ሁሉንም ዜጋ ለማሳተፍ የጀመረው የሕዝብ ንቅናቄ ነው:: ግንባታው ተጀምሯል ለማለት የሚያስደፍሩ መረጃዎችን ጉዳዩ የሚመለከታቸው ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች መግለጫዎችን በተለያዩ ሚዲያዎች ሰጥተዋል:: በመስጠትም ላይ ይገኛሉ:: ግንባታውን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር ሲታይ የሚጠይቀው መስዋዕትነት ቀላል አይሆንም::

ታላቁን የዓባይ ግድብ አስመልክቶ አብዛኛዎቹ ባለሙያዎች በተለያዩ ሚዲያዎች የሚሰጧቸው መግለጫዎች ያተኮሩት በምህንድስናውና በኃይል አቅርቦቱ ዘርፍ ላይ ነው:: የሕዝቡም ግንዛቤ እንደዚሁ የሚቀጥል ይመስላል:: አልፎ አልፎም ከታችኛው ተፋሰስ አገሮች ጠቀሜታ ጋር በተያያዘ ከሚሰጡት ማብራሪያዎች ውስጥ "ደለል ይቀርላቸዋል፣ ጎርፍ ይቀንስላቸዋል፤" የሚሉ ይገኙበታል:: ለእነርሱም ቢሆን መልካም ማሰብ ጥሩ ነው::

በእኔ ግምትና ብዙዎችም እንደሚስማሙብት የሚሊኒየሙ ግድብ አሁን ያለውን ትውልድ አልፎ በርካታ ቀጣይ ትውልዶችን ታሳቢ የሚያደርግ፣ የውኃውንም ዘላቂና ፍትሐዊ አጠቃቀም ከግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባዋል:: እስከዛሬ ድረስ በአገራችን የተገነቡት ግድቦች የወንዞቹን ተፋሰስ ልማትና በተፋሰሱ ውስጥ ያለውን ነዋሪ ሕዝብ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ፣ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄደውን ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር ግምት ውስጥ ያላስገቡ እንደነበሩ ይታወቃል:: አንዳንዶቹ ግድቦች ለግንባታቸው የወጣውን ያህል ተመጣጣኝ አገልግሎት ሳይሰጡ በአጭር ጊዜ በደለል ሊሞሉ የመቻላቸው ጉዳይ (ለአብነት ግልገል ጊቤን ይጠቅሷል) በየጊዜው እየጨመረ ከሚመጣው የኃይል ፍላጎት ጋር ሲወዳደር ትልቅ ስጋት የሚፈጥርና እርምትም የሚፈልግ እንደሆነ ይታወቃል::

ካለፉት ግድቦች የተገኘውን ትምህርት ግምት ውስጥ ማስገባት በተለይ የሚሊኒየሙ ግድብ ከሚጠይቀው የገንዘብና ሌላም ሀብት አንፃር የተለየ ትኩረት የሚሻ ነው:: ወደ 63 ቢሊዮን ሜትር ኩብ የሚገመተው የግድቡ ውኃ የዓባይ ተፋሰስ የሚዳስሳቸው ተራሮችና ሸንተረሮች ተገቢው የአፈርና የውኃ ጠበቃ ሥራ ካልተሠራባቸው፣ ወይም የአካባቢ ጥበቃና ልማት ሥራዎች ተጠናክረው ካልተካሄዱባቸው ግድቡ ከ30 ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ በደለል ሊሞላ ይችላል:: ዓባይ ተሸክሞ ወደ ታችኛው ተፋሰስ አገሮች የሚያሻግረው አፈር በየዓመቱ እስከ ሁለት ቢሊዮን ቶን የሚገመት በመሆኑ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ልማቱ ሥራ ከግድቡ ግንባታ ባላነሰ ትኩረት የሚሰጠው ከሆነ፣ የአፈር መሸርሸርንና የግድቡን በደለል የመሞላት ሁኔታ መቀነስ ብሎም ማስቀረት ብቻ ሳይሆን በተፋሰሱ ውስጥ የሚገኘውን ሕዝብ የማምረት አቅም በማሳደግ ወደ ተሻለ ኑሮ ያሸጋግረዋል::

መንግሥት በግድቡ ግንባታ ዙሪያ ያነሳሳው ሕዝባዊ ንቅናቄም በተፋሰሱ ዙሪያም ልዩ ግምት በመስጠት በዘመቻ ሳይሆን፣ በተጠናና በተቀናጀ መልኩ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ ከግንባታው ጎን ለጎን እንዲካሄድ አስፈላጊውን ስልት መቀየስና እንዲተገበርም መምራትና አወንታዊ ጫናም መፍጠር ይጠበቅበታል:: ይህ ማለት አሁን በተለያዩ ቦታዎች ከተጀመሩት ለተፈጥሮ ሀብት ትኩረት ከመስጠት በበለጠ ሁኔታ ማለት ነው:: ከዚህ ባለፈ ከእኛ አልፎ ለታችኛው ተፋሰስ አገሮችም ዘላቂ የውኃ አጠቃቀም ይኖር ዘንድ፣ ይልቁንም በኢትዮጵያ ለሚካሄደው የተፈጥሮ ሀብት ልማት አጋር በመሆን ድርሻ እንዲኖራቸውና ለእነርሱም በመጠንም ሆነ በጥራት የተሻለ ውኃ ስለማግኘታቸው የማሳመን ትልቅ ዲፕሎማሲያዊ ሥራ መሥራት ይጠበቅብናል::

> በእኔ ግምትና ብዙዎችም እንደሚስማሙበት የሚሊኒየሙ ግድብ አሁን ያለውን ትውልድ አልፎ በርካታ ቀጣይ ትውልዶችን ታሳቢ የሚያደርግ፣ የውኃውንም ዘላቂና ፍትሐዊ አጠቃቀም ከግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባዋል:: እስከዛሬ ድረስ በአገራችን የተገነቡት ግድቦች የወንዞቹን ተፋሰስ ልማትና በተፋሰሱ ውስጥ ያለውን ነዋሪ ሕዝብ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ፣ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄደውን ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር ግምት ውስጥ ያላስገቡ እንደነበሩ ይታወቃል:: አንዳንዶቹ ግድቦች ለግንባታቸው የወጣውን ያህል ተመጣጣኝ አገልግሎት ሳይሰጡ በአጭር ጊዜ በደለል ሊሞሉ የመቻላቸው ጉዳይ (ለአብነት ግልገል ጊቤን ይጠቅሷል) በየጊዜው እየጨመረ ከሚመጣው የኃይል ፍላጎት ጋር ሲወዳደር ትልቅ ስጋት የሚፈጥርና እርምትም የሚፈልግ እንደሆነ ይታወቃል::

ግድቡም ከኃይል ምንጭነት ባሻገር በቀጥታ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የአሣ ሀብት ልማትን በማካተትና ከፍተኛ የቱሪዝም መስህብም ሆኖ ሊያገለግል የሚችልበት ሰፊ ዕድልም እንዳለ መታሰብ ይኖርበታል::

ለማጠቃለል በድኅነት፣ በረሃብና በእርስ በእርስ ጦርነት አገሮች የምትታወቅበት ታሪኳ ከፍ ብሎ፣ በአጎራባቾቿና በተፋሰሱ የታችኛው አገሮች የሚሰጣት ግምት ከፍ ብሎ፣ አሁን ያለው ትውልድ ኑሮ እንዲሻሻልና ለቀጣይ ትውልዶችም የተሻለ ብሩኅ ተስፋ ለማስጨበጥ የመንግሥትም ሆነ የሕዝቡ የአመለካከት አድማስ ሊሰፋ ይገባል:: ይህን ማድረግ ከቻልን አባይ ለአገሩም ልጆች ሆነ ለታችኛው ተፋሰስ አገሮች የትብብርና የሰላም መሠረት ይሆናል:: እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!